# የሐዋርያት አመክንዮ (አመክንዮ ዘሐዋርያት)

1) የጌታችንና የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት በሚኾን፥ ፍጥረትን ኹሉ በፈጠረ፥ በአንድ አምላክ እናምናለን።

ለህላዌው (ለአኗኗሩ) ምክንያት የለውምና፥ አስቀድመን እንደ ተናገርን በዘመን ኹሉ ይኖራል እንጂ መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የለውም። በእርሱም የማይጠፋ ብርሃን አለ፤ ወደ እርሱ ለመቅረብም የሚቻለው የለም። ብቻውን የሚኖር አንድ መለኮት ነው እንጂ፥ በመለኮት ሁለት ወይም ሦስት ወይም ከዚያ በላይ አይደለም። ኹሉን የያዘና በፍጥረቱም ኹሉ ላይ የሠለጠነ መሆኑን በኦሪትና በነቢያት ተረድተን ያወቅነው እንጂ፥ የማይታወቅ የተሠወረ አይደለም እኮ ከእርሱ ጋር የተካከለ፥ ሹመታትንና ሥልጣናትን ኹሉ የፈጠረ፥ ዓለም ሳይፈጠር የተወለደ አንድያ ልጅ የሚሆን፥ የጌታችንና የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር አንድ ነው።

2) ጌታችንም በኋለኛው ዘመን ሰው ይሆን ዘንድ ወደደ፤ ያለዘርዐ ብእሲ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን ነሣ፤ ያለ ኀጢአትና ያለ በደል እንደ ሰው አደገ፤ በአንደበቱም ምንም ሽንገላ አልተገኘም። ከዚህም በኋላ በሥጋው መከራን ተቀበለ፤ ሞተም፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። ወደ ላከውም ወደ አብ ወደ ሰማያት ዐረገ። በኀይልም ቀኝ ተቀመጠ።

3) በአብና በወልድ ዘንድ ህልው የሚኾነውን፥ ዓለምን ያዳነውንና ከአብ የሠረጸውን የእውነት መንፈስ ጰራቅሊጦስን ሰደደልን።

4) እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍጥረት ኹሉ መልካም እንደ ኾነ ግድፈትም እንደሌለበት እንናገራለን (ማቴ. 10፥28)። የሥጋ ሕይወት የምትሆን መንፈስ ግን ኹለመናዋ ንጽሕትና ቅድስት ናት። (ኍ. 16፥22፤ ኢዮ. 12፥10፤ 32፥8፤ 1ተሰ. 5፥23)

5) እኛስ ጋብቻ ንጹሕ እንደ ሆነ መዋለድም ርኩሰት እንደሌለበት እንናገራለን፤ እግዚአብሔር ሕዝብ ይበዙ ዘንድ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮአቸዋል። (ዘፍ. 1፥26-28፤ ሚል. 2፥15-16፤ ዕብ. 13፥4)

6) ከሥጋ ጋር የማትሞትና የማትጠፋ ነፍስ በሥጋችን ውስጥ እንዳለች እናስተውል (ማቴ. 10፥28 )። እኛ ግን ሃይማኖትን የካዱት በእኛ ዘንድ የረከሱ ናቸውና፥ መለያየትን፥ ሕገ ወጥ መሆንንም ኹሉ እንጸየፋለን። (2ዮሐ. 1፥9-11፤ 2ጢሞ. 3፥1-9 )

7) ዳግመኛም የጻድቃንና የኃጥኣን የሙታን ትንሣኤ እንዳለ፥ ኹሉ እንደ ሥራው መጠን ፍዳውን የሚቀበልበት የፍርድ ቀን እንዳለ እናምናለን። (ራእ. 20፥11-13)

8) ዳግመኛም ክርስቶስ የአብ ሊቀ ካህናት ሆኖ የሰውን ወገን ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀ፥ በእውነት ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ፥ ሰው በመሆኑ ምንም ሕጸጽ እንደሌለበት እናምናለን። (ዕብ. 7፥18፤ ገላ. 5፥6፤ 6፥15)

9) እንግዲህ እንደ አይሁድ አንገዘር (ዕብ. 7፥18፤ ገላ. 5፥6፤ 6፥15)፤ ኦሪትንና ነቢያትን የሚፈጽማቸው እንደ መጣ እናውቃለንና (ዕብ. 7፥18፤ ገላ. 5፥6፤ 6፥15)፤ አሕዛብ ኹሉ መምጣቱን በተስፋ የሚጠባበቁት ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ከአይሁድ፥ ከዕሤይም ሥር የተገኘ ነው። (ዕብ. 7፥18፤ ገላ. 5፥6፤ 6፥15)
ሥልጣኑም በትከሻው ላይ ነው። (ዕብ. 7፥18፤ ገላ. 5፥6፤ 6፥15)
ለእርሱም ምስጋና፥ ገናንነት፥ ክብር፥ ባርኮት፥ ውዳሴና ማሕሌት ይገባዋል። ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙም፤ አሜን።